
# በሀረሪ ሕዝብ ክልላዊ መንግስት የ2014 በጀት ዓመት
# ለዜጎች የተዘጋጀ የበጀት መረጃ




የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ቢሮ
ሀረር / ኢትዮጵያ

## 1. የኃላፊ መልዕክት

የክልሉን ነባራዊ ሁኔታ ያገናዘበ የኢኮኖሚ ሥርዓት በመከተል የግል ዘርፉን ጉልህ ሚናና ተሳትፎ በማሳደግ የበለጸገች ክልልን መገንባት፤ የተረጋጋ የማክሮ ኢኮኖሚ ሁኔታን በመፍጠር ፈጣንና ዘላቂነት ያለው የኢኮኖሚ ዕድገት ማስመዝገብና ሰፊ የሥራ ዕድል በመፍጠር፤ አጠቃላይ የኢኮኖሚ ምርታማነትን፣ ጥራትንና ተወዳዳሪነትን በማጎልበት የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ለውጥ ማረጋገጥ፣ የማኅበራዊና የመሠረተ ልማት ጥራትንና ተደራሽነትን በማረጋገጥ ዜጎች የልማቱ ባለቤትና ፍትሐዊ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ ነው፡፡ የበጀት ስርዓት ግልፅነትንና ተጠያቂነትን ከተላበሰ ዜጎች የሀገራቸውን የኢኮኖሚ ሁኔታና የበጀት ፖሊሲዎችን መረጃ የማግኘት እድላቸው እንዲሰፋ ያደርጋል፡፡ ለዜጎች የሚገለፀው የበጀት መረጃ የተሟላ፤ ትክክለኛ፤ ወቅታዊ እና የመረጃ አቅርቦቱ ቀጣይነት ያለውና በማራኪ ሁኔታ መቅረብ ይኖርበታል፡፡ የፋይናንስ ግልጽነትና ተጠያቂነት ዓላማ የበጀትና የአገልግሎት አሰጣጥ ደረጃ መረጃን ለዜጎች ተደራሽ በማድረግና ግንዛቤ በመፍጠር ዜጎች ደረጃውን የጠበቀ መሰረታዊ አገልግሎት እንዲያገኙ እና በመንግስት በጀት ቀጥተኛ ተጠቃሚነታቸውን ማሳደግ ነው ፡ስለ መንግስት አሰራር እና የዜጎች መረጃን የማግኘት መብትን በተመለከተ በህገ መንግስቱ የተደነገጉ ድንጋጌዎች **አንቀፅ 12 ላይ** «የመንግስት አሰራር ግልፅ በሆነ መንገድ መከወን አለበት በማለት ይደነግጋል» ፡፡

ይህንኑ የግልጽነትና ሁለንተናዊ የዜጎች ተሳትፎን በማጠናከር በመንግስት በጀት አፈጻጸም ላይ የተጠያቂነት ስርዓቱ ተፈጻሚነት ተጠናክሮ እንዲቀጥል የገንዘብ እና ኢኮኖሚ ትብብር ቢሮ ለ2014 በጀት ዓመት የጸደቀዉ በጀት መሰረት በማድረግ ሁሉም የሀገሪቱ ዜጋ በቀላሉ ተረድቶት በትግበሩ ሂደቱ ላይ በሙሉ አቅሙ ተሳታፊና ተጠቃሚ መሆን የሚያስችል የዜጎች በጀት መረጃ ሰነድ ተዘጋጅቷል፡፡ በጀቱም የ10 ዓመት የዘላቂ የልማት ዕቅድን ታሳቢ ያደረገ ነዉ፡፡ ስለሆነም ይህ የዜጎች በጀት መረጃ ሰነድ በተፈቀደው የመንግስት የገቢና የወጪ ዕቅዶች ውስጥ የተካተተውን በጀት ማህበረሰቡ በቀላሉ ተረድቶና ተጠቅሞ በመንግስት የልማት ስራዎች ላይ ተሳትፎዉን በማጠናከር የተጠያቂነት ስርዓት ማስፈን እንዲቻል ሚናቸዉን እንዲወጡ ጥሪዬን ማስተላለፍ እወዳለሁ፡፡

## 2. መግቢያ

ዜጎች ስለከፈሉት ግብር፣ መንግስት የሰበሰበዉን ገቢ በምን አኳኋን ወጪ እንዳደረገ ማወቅና የመሰረታዊ አገልግሎቶች አሰጣጡም ቀልጣፋና ዉጤታማ እንዲሆን ይፈልጋሉ፡፡ መንግስትም በየደረጃዉ የአስተዳደር እርከኖች የዜጎችንና የሲቪክ ማህበራት የመረጃ ተደራሽነትንና ተሳትፎ በማሳደግ የመሰረታዊ አገልግሎት አሰጣጡ ግልጽነት የሰፈነበትና የተጠያቂነት ስርዓቱ ተፈጻሚነት ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡ ይህንኑ ተፈጻሚ ለማድረግ በመንግሰት አጠቃላይ የፋይናንስ አስተዳደር መረጃ በቀላልና ለሁሉም ሊገባ በሚችል እንዲሁም ተደራሽነት ባለዉ መልኩ ለማቅረብ የዜጎች በጀት ሰነድ መዘጋጀትና ማሰራጫት እንዳለበት ታምኖበታል፡፡

## 3. መንግስት የዜጎች በጀት ሰነድን ለምን ይዘጋጃል?

መንግስት ከተለያዩ የገቢ ምንጮች በሰበሰበዉ ሀብት ተጠያቂነት እንዳለበት ሁሉ ስለ አጠቃላይ በጀት መረጃ ለሁሉም ሊገባ በሚችል መልኩ አዘጋጅቶ በማሰራጨት ዜጎችም ባገኙት መረጃና ግንዛቤ መሰረት በዕቅዶችና በአፈጻጸሞች ላይ ተሳታፊ እንዲሆኑ ማስቻል ይኖርበታል፡፡ ዜጎች የመንግስት በጀት ምንጭና ተጠቃሚም እንደመሆነቸዉ መጠን አጠቃላይ የበጀት ሂደቱና ዝግጅት መረጃ ለሁሉም ተደራሽነት ባለዉና ሊገባ በሚችል መልኩ ተዘጋጅቶ የመንግስት የትግበራ ዕቅዶች ዝርዝር፣የታቀዱት እንዴት እንደሚሰሩ፣ ማን እንደሚያስፈጽማቸዉ፣ምን ያህል ወጪ እንደሚደረግባቸዉና በወጣዉ ወጪ ልክ የአገልግሎት አሰጣጡ ተፈጻሚ ስለመሆኑ በመቆጣጠር ተጠያቂነትን ማረጋገጥ ይኖርባቸዋል፡፡

መንግስት ለዜጎች ተጠያቂነትን ለማረጋገጥ በበጀት ዓመቱ በሁሉም ደረጃ በሚገኙ የስልጣን እርከኖች ተዘጋጅተዉና በህዝብ ተወካዮች ጸድቀዉ ስራ ላይ እንዲዉሉ የሚደረጉ በጀቶች ለሁሉም ሊገባ በሚችል መልኩ የዜጎች በጀት መረጃ ሰነድ አዘጋጅቶ ተደራሽ ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡

## 4. በጀት በማን ይጸድቃል

የክልሉ በጀት በክልሉ ምክር ቤት የሚጸድቅ ሲሆን የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ቢሮ አማካኝነት ለእያንዳንዱ ለተፈቀደለት የመንግስት ተቋም በማሳወቅ ለተፈቀደለት አላማ ስራ ላይ እንዲውል ይደረጋል፡፡

## 5. የዜጎች በጀት መረጃ በማን ይዘጋጃል?

የዜጎች በጀት መረጃ ሰነድ በሀገር ደረጃና በክልል/ከተማ አስተዳደር ደረጃ የሚዘጋጅ ሲሆን፤ የገንዘብ ሚኒስቴር ሀገራዊዉና በፌዴራል ደረጃ ያለዉን ጥቅል የበጀት መረጃ ለሁሉም ሊገባ በሚችል መልኩ የሚዘጋጅ ሲሆን በክልል ደረጃ የክልሉ ገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ቢሮ ያዘጋጃል፡፡

## 6. ዓላማ

የዜጎች በጀት ሰነድ ዝግጅት ዋና ዓላማ አጠቃላይ የበጀት መረጃን ሁሉም በቀላሉ ሊረዳ በሚችል መልኩ በማዘጋጀት የዜጎችንና የሲቪክ ማህበራት በመንግስት በሚሰሩ ተግባራት ላይ ታሳታፊ በመሆን የሚጠበቅባቸዉን እንዲወጡ ማድረግ ነዉ፡፡

## 7. የመንግስት በጀት ምንድን ነው?

በጀት ማለት ገቢን ከየትና እንዴት እንደሚሰበሰብ ፣ የተሰበሰበው ገቢ እንዴት እና ለምን እንደምናውልው የሚያሳይ የገቢና ወጪ ዕቅድ ነው ፡፡ በመሆኑም ስትራቴጂክ ዕቅድን ለመተግበር ለእያንዳንዱ ክፍል ስልጣንና ተጠያቂነትን ይሰጣል ተሳትፎንም ይጨምራል ፡፡


ይህ ማለት ህብረተሰቡ በጀት የት ? ለምን ? እንዴት? የመሳሰሉ ጥያቄዎችን ጠይቆ የመረዳት መብቱ የተጠበቀ በመሆኑ በበጀት ዝግጅት ሂደት እንዲሳተፉ ማድረግና ኃላፊነቱን ተገንዝቦ አፈፃፀሙን በባለቤትነት እንዲቆጣጠር በማበረታታት ተሳትፎን መጨመር ማለት ነው ፡፡

ከበጀቱ አመዳደብ ስርዓት ውስጥ ዋናው የወጪ በጀት ሲሆን የወጪ በጀት አይነቶች ሁለት ናቸው ፡፡ አንደኛው የመደበኛ ወጪ በጀት ሲሆን መንግስት ለሚያከናውናቸው አስዳደራዊ ፣ ማህበራዊ ፣ ኢኮኖሚያዊና ለጠቅላላ አገልግሎት / የስራ ክፍል / ለሚያስፈልጉ ደመወዝና ስራ ማስኬጃ ወጪዎች የሚመደበው በጀት ነው ፡፡ ሁለተኛ የካፒታል ወጪ በጀት ነው ፡፡ ይህም ለፕሮጀክት የሚመደብና በውስጡ እነዚህን ተግባራዊ ከማድረግ ጋር የተያያዙትን የደመወዝና ስራ ማስኬጃ ወጪዎችን ይጨምራል፡፡ የካፒታል በጀቶች ረጅም ዕድሜ ላላቸው ንብረቶች ፣ ህንፃ ፣ ውሃ ጉድጓድ ቁፋሮ ፣ መንገድ ለመሳሰሉት የግንባታ ስራዎች የሚውሉ ወጪዎችን ይይዛል ፡፡

## 8. የበጀት ሂደቶች (BUDGET PROCESS)

የመንግስት በጀት ሂደት በበጀት ካሌንደር ላይ በግልፅ እንደተቀመጠው አራት ደረጃዎች አሉት እነሱም እንደሚከተለው ይሆናሉ፡፡

1. **የበጀት ዝግጅት ምዕራፍ፡-** የበጀት ዝግጅት መቼ መዘጋጀት እንዳለበትና በማን መዘጋጀት እንዳለበት የሚብራራበት ሂደት ነው፡፡
2. **በጀትን ማፀደቅ**፡- ይህም ሂደት በገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ቢሮ ለክልሉ ምክር ቤት ቀርቦ በጀትን የሚያፀድቅበት ሂደት ነው፡፡
3. **የትግበራ ምዕራፍ**፡- ማለት ባለበጀት አካላት ተግባራዊ ወይም ፈፃሚ አካላት የተመደበላቸውን በጀት ወደ ተግባር የሚያውሉበት ሂደት ነው፡፡
4. **የበጀት ግምገማ**፡- ማለት ተግባር ላይ የዋለውን የመንግስት በጀት ተቆጣጣሪ አካላት ማለትም ዋና ኦዲትና የህዝብ ተወካዮች ም/ቤት ሥራ ላይ መዋሉን የሚያረጋግጡበት ምዕራፍ ነው፡፡



## 9. የገቢ አይነቶች

በዚህ አንጻር የሐረሪ ክልል ገቢ ከተለያዩ የገቢ ምንጮች የተገኘ ሲሆን ከነዚህም ውስጥ፡-

9.1.**ቀጥታ ታክስ** /Direct Taxes/ የግለሰብ ገቢ ግብር፣ የኪራይ ገቢ፣ የንግድ ትርፍ ገቢ ግብር፣ ዊዝ ሆልድ ታክስ.... / ሲሆኑ፤

9.2. **ቀጥታ ካልሆኑ ታክስ**/ Indirect Taxes/ ተጨማሪ እሴት ታክስ፣ ኤክሳይዝ ታክስ፣ ተርን ኦቨር ታክስ፣ታክስ ያልሆኑ ገቢዎች / Administrative fees and charges, Sales of Public Goods and Services/ ናቸው፡፡

9.3.**ማዘጋጃ ቤታዊ ታክስ ገቢ** /Municipal Taxes/ ማዘጋጃ ቤታዊ ታክስ እና ማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎቶች፤

9.4. **ከአለም ባንክ ፡-** በዕርዳታና ብድር የሚገኙ ገንዘቦች

9.5. ከፌደራል መንግስት የሚሰጥ ድጎማ ናቸው፡፡

## 10. የክልሉ 10 ዓመት ዕቅድ የትኩረት አቅጣጫዎች


የ2014 በጀት የተመደበው ክልሉ በ10 ዓመት ስትራቴጂክ ዕቅዱ ያስቀመጣቸውን የትኩረት አቅጣጫዎች ለማሳካት ታሳቢ በማድረግ ከዚህ በታች የተዘረዘሩት የሀረሪ ክልላዊ መንግስት የትኩረት አቅጣጫዎች ናቸው እነሱም

- በክልሉ ጥራት ያለው የኢኮኖሚ ዕድገት ማረጋገጥ
- በክልሉ የኢኮኖሚ ምርታማነት እና ተወዳዳሪነት ማረጋገጥ
- በክልሉ ዘላቂ ሰላም እና ጠንካራ ቀጠናዊ ኢኮኖሚዊ ትብብር ማረጋገጥ
- የፍትህ ተደራሽነት እና ውጤታማ የህዝብ አገልግሎት ማረጋገጥ
- የልማት ተጠቃሚነት እና ማህበራዊ አካታችነት ማረጋገጥ
- ሰው ሰራሽና ተፈጥሮዊ አደጋዎችን የሚቋቋም አረንጎዴ ኢኮኖሚ ማረጋገጥ
- የግሉን ዘርፍ ኢኮኖሚ መሪነት ማረጋገጥ
- ዘላቂ የልማት ፋይናንስን ማረጋገጥ
- የቴክኖሎጂ አቅምና የዲጂታል ኢኮኖሚ ግንባታ

## የሀረሪ ክልል መንግስት 2014 በጀት ዓመት ገቢ

| ተቁ | የገቢ ዝርዝር | የብር መጠን |
|---|---|---|
| 1 | **መደበኛ ገቢዎች** | **1,064,740,754** |
| 1.1 | ታክስ ነክ ገቢዎች | 543,534,725.00 |
| 1.2 | ቀጥታ ያልሆኑ ታክስ | 310,225,923.00 |
| 1.3 | ታክስ ያልሆኑ ገቢዎች | 92,670,229.00 |
| 1.4 | ማዘጋጃ ቤታዊ ገቢ | 118,309,877.00 |
| 2 | **ከፌዴራል መንግስት ድጎማ** | **1,652,207,038.00** |
| 2.1 | ከመንግስት ግምጃ ቤት | 1,505,249,463.00 |
| 2.2 | ከውጭ እርዳታ | 55,757,575.00 |
| 2.3 | ለዘላቂ ልማት ግቦች ማሳኪያ | 91,200,000.00 |
| 3 | ቻናል አንድ ፕሮግራም | 180,612,582.00 |
| 4 | ከአለም ባንክ UIIDP የተገኘ | 95,674,641.00 |
| | **ጠቅላላ የገቢ ድምር** | **2,993,235,015.00** |


## 12. የ2014 ዓ/ም አጠቃላይ የክልሉ በጀት




የሀረሪ ክልል በ2014 በጀት ዓመት የልማት ሥራዎችን ለማከናወን በአጠቃላይ ብር 2,993,235,015 (**ሁለት ቢሊዮን ዘጠኝ መቶ ዘጠና ሶስት ሚሊዮን ሁለት መቶ ሰላሳ አምስት ሺህ አስራ አምስት ብር**) በጀት የተያዘ ሲሆን ከዚህ ውስጥ ለመደበኛ በጀት ብር 1,455,196,171 (**አንድ ቢሊዮን አራት ሃምሳ አምስት ሚሊዮን አንድ መቶ ዘጠና ስድስት ሺህ አንድ መቶ ሰባ አንድ ብር**) ለክልሉ ደመወዝና ሥራ ማስኬጃ የተመደበ በጀት ነው፡፡ በተጨማሪም ለካፒታል በጀት የተመደበ ብር 1,143,441,744 (**አንድ ቢሊዮን አንድ መቶ አርባ ሶስት ሚሊዮን አራት መቶ አርባ አንድ ሺህ ሰባት መቶ አርባ አራት ብር**) ሲሆን ይህም በክልሉ ለተጀመሩ ነባር ፕሮጀክቶች ማስጨረሻ እና ለአዳዲስ ፕሮጀክቶች ማስፈፀሚያ የሚሆን ነው፡፡ ፤ ከማዘጋጃ ብር 118,309,877 (አንድ መቶ አስራ ስምንት ሚሊዮን ሶስት መቶ ዘጠኝ ሺህ ስምንት መቶ ሰባ ሰባት ብር) እንዲሁም ከእርዳታ ብር 276,287,223 (ሁለት መቶ ሰባ ስድስት ሚሊዮን ሁለት መቶ ሰማኒያ ሰባት ሺህ አስራ አምስት ብር) ከላይ የተቀመተው በጀት እንደሚያሳየው ክልሉ ከፍተኛ የሆነ በጀት ለካፒታል ፕሮጀክቶች መመደቡ በክልሉ ያለውን የልማት ጥያቄ ለመመለስና በ10 ዓመት ዕቅዱ ላይ የተቀመጡትን የትኩረት አቅጣጫዎች ለማሳካት ከፍተኛ የሆነ ትኩረት መስጠቱን የሚያሳይ ነው፡፡

## 13. ለሀረሪ ክልላዊ መንግስት ለመሠረታዊ አገልግሎት ሴክተር በ2014 ዓ.ም የተመደበ ካፒታልና መደበኛ በጀት

| ተ.ቁ | የሴክተሩ ሥም | መደበኛ በጀት | ካፒታል በጀት | ድምር |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ግብርና | 33,869,819.00 | 115,087,982.00 | 148,957,801.00 |
| 2 | ትምህርት | 170,957,929.00 | 123,317,059.00 | 294,274,988.00 |
| 3 | ጤና | 130,911,516.00 | 62,875,679.00 | 193,787,195.00 |
| 4 | ውሃ | 44,165,038.00 | 65,001,546.00 | 109,166,584.00 |
| 5 | መንገድ | 25,275,098.00 | 173,505,939.00 | 198,781,037.00 |
| **ጠቅላላ ድምር** | | **405,179,400.00** | **539,788,205.00** | **944,967,605.00** |


ለሀረሪ ክልላዊ መንግስት ለመሠረታዊ አገልግሎት ሴክተር በ2014 በጀት አመት
የተመደበ ካፒታልና መደበኛ በጀት
180,000,000.00
160,000,000.00
140,000,000.00
120,000,000.00
100,000,000.00
80,000,000.00
60,000,000.00
40,000,000.00
20,000,000.00
0.00
የተመደበ ብር መጠን
መደበኛ በጀት
ካፒታል በጀት


ለሀረሪ ክልላዊ መንግስት ለመሠረታዊ አገልግሎት ሴክተር
በ2014 በጀት አመት የተመደበ በጀት ያላቸው ድርሻ
16%
31%
20%
12%
21%
ግብርና
ትምህርት
ጤና
ውሃ
መንገድ

## 14. ለክልሉ መንገድ ዘርፍ የተመደበ በጀት

**ለመንገድ ብር 198,781,037.00**









# 15. ለክልሉ ግብርና ዘርፍ የተመደበ በጀት


**ለግብርና ብር 148,957,801.00**





# 16. ለክልሉ ትምህርት ዘርፍ የተመደበ በጀት

**ለትምህርት ብር 294,274,988.00**










## 17. ለውሀ ዘርፍ የተመደበ በጀት

# ለውሃ ብር 109,166,584.00







## 18. ለክልሉ ጤና ዘርፍ የተመደበ በጀት

**ለጤና ብር 193,787,195.00**







የክልሉ መንግስት ለድህነት ተኮር ሴክተሮች ከፍተኛ የሆነ ትኩረት በመስጠት የህብረተሰቡን የኑሮ ሁኔታ ለማሻሻልና መሰረታዊ አገልግሎቶችን በተሳካ ሁኔታ ተደራሽ ለማድረግ ከፍተኛ የሆነ በጀት መድቦ እየሰራ ሲሆን ከላይ በሰንጠረዥ ላይ እንደምንመለከተው ለትምህርት፣ለጤና፣ለውሃ፣ለመንገድና ለግብርና ዘርፎች ከፍተኛ የሆነ በጀት በመመደብ ወደ ሥራ ተገብቷል፡፡ ከጠቅላላ ለመሰረታዊ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ከተመደበው በጀት ውስጥ ከፍተኛውን ድርሻ የሚይዘው የካፒታል ፕሮጀክት ሲሆን ይህም ብር 539,788,205 (አምስት መቶ ሰላሳ ዘጠኝ ሚሊዮን ሰባት መቶ ሰማኒያ ስምንት ሺህ ሁለት መቶ አምስት ብር) ለልማት እንደሚውል የሚያሳይ ነው፡፡ ለመደበኛ በጀት የተመደበው ማለትም ለሥራ ማስኬጃና ለደመወዝ የተመደበው ብር 405,179,400 (አራት መቶ አምስት ሚሊዮን አንድ መቶ ሰባ ዘጠኝ ሺህ አራት መቶ ብር) ሲሆን ይህም ከካፒታል በጀት አንፃር ሲታይ አነስተኛ ነው፡፡


## 19. በ2014 ዓ.ም ለደመወዝ፣ሥራ ማስኬጃ፣ለካፒታል እና ለዘላቂ ልማት ግቦች የተመደበ በጀት

አጠቃላይ ለሀረሪ ክልል የተመደበ የ2014 በጀት አመት መደበኛና ካፒታል ከዚህ በታች ሰንጠረዥ ላይ እንደተገለጸው የክልሉ ለመደበኛ የተመደበ በጀት 57% ሲሆን 37% የሚሆነው ለካፒታል በጀት ነው።

| ተ.ቁ | የበጀቱ ዓይነት | አጠቃላይ በጀት | በ% |
|---|---|---|---|
| 1 | ደመወዝ | 1,013,365,620.00 | 40 |
| 2 | ሥራ ማስኬጃ | 441,830,551.00 | 17 |
| 3 | ካፒታል በጀት | 953,416,669.00 | 37 |
| 3.1 | ለዘላቂ ልማት ግቦች ማሳኪያ | 91,200,000.00 | 4 |
| 3.2 | የውጭ አገር እርዳታ | 55,757,575.00 | 2 |
| | ጠቅላላ ድምር | 2,555,570,415.00 | 100 |

## 20. አጠቃላይ የ2014 ዓ.ም ካፒታል፣ መደበኛ በጀትና የውጭ ሀገር ዕርዳታ


| ተ.ቁ | የበጀቱ ዓይነት | አጠቃላይ በጀት | በ% |
|---|---|---|---|
| 1 | መደበኛ በጀት | 1,455,196,171.00 | 57 |
| 2 | ካፒታል በጅት | 953,416,669.00 | 37 |
| 3 | ለዘላቂ ልማት ግቦች ማሳኪያ | 91,200,000.00 | 4 |
| 4 | የውጭ ሀገር እርዳታ | 55,757,575.00 | 2 |
| | ጠቅላላ ድምር | 2,555,570,415.00 | 100 |




ከላይ ቻርቱ ላይ እንደተቀመጠው ለሀረሪ ክልል ከውጭ ሀገር ዕርዳታ ይገኛል ተብሎ የተቀመጠው በ2014 በጀት ዓመት ብር 55,757,575 (**ሃምሳ አምስት ሚሊዮን ሰባት መቶ ሃምሳ ሰባት ሺህ አምስት መቶ ሰባ አምስት ብር**) ሲሆን ከአጠቃላይ በጀት ያለው ድርሻ በፐርሰንት ሲታይ 2% ነው።

## 21. ለወረዳና ክልል ሴክተር ቢሮዎች የተመደበ የ2014 መደበኛና ካፒታል በጀት

| ተ.ቁ | መግለጫ | ደመወዝ | ሥራ ማስኬጃ | ካፒታል በጀት | ድምር |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ለሴክተር ቢሮ | 582,967,883 | 337,804,671 | 893,416,669 | 1,814,189,223 |
| 2 | ለወረዳዎች | 381,487,194 | 63,959,780 | 60,000,000 | 505,446,974 |
| | **ጠቅላላ በጀት** | **964,455,077** | **401,764,451** | **953,416,669** | **2,319,636,197** |



የክልሉ መንግስት ከፍተኛ የሆነ በጀት ለክልል ሴክተር ቢሮዎች በ2014 በጀት ዓመት የመደበ ሲሆን ይህም ብር 1,814,189,223 ( አንድ ቢሊዮን ስምንት መቶ አስራ አራት ሚሊዮን አንድ መቶ ሰማኒያ ዘጠኝ ሺህ ሁለት መቶ ሀያ ሶስት ብር) ነው፡፡ ለወረዳዎች የተመደበው በጀት ብር 505,446,974 (አምስት መቶ አምስት ሚሊዮን አራት መቶ አርባ ስድስት ሺህ ዘጠኝ መቶ ሰባ አራት ብር) ሲሆን ከዚህ ውስጥ ለደመወዝ የተመደበው በጀት ብር 381,487,194 (ሶስት መቶ ሰማኒያ አንድ ሚሊዮን አራት መቶ ሰማኒያ ሰባት ሺህ አንድ መቶ ዘጠና አራት ብር) ነው፡፡ ለክልል ሴክተር ቢሮዎች ከተመደበው በጀት ውስጥ ከፍተኛውን ድርሻ የሚይዘው ካፒታል በጀት ሲሆን ይህም ብር 893,416,669 (ስምንት መቶ ዘጠና ሶስት ሚሊዮን አራት መቶ አስራ ስድስት ሺህ ስድስት መቶ ስልሳ ዘጠኝ ብር) ነው፡፡ ይህም ማለት ከፍተኛ የሆነ አዲስና ነባር ፕሮጀክቶችን ለመስራት የተያዘ መሆኑን ያሳያል ማለትም ክልሉ ከፍተኛ የሆነ የመሠረተ ልማትና ግንባታ ሥራዎችን ለማከናወን ይጠቀምባቸዎል ማለት ነው፡፡

## 22. መረጃ ማግኛ አድራሻ

ይህ ሰነድ በሀረሪ ክልል ገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ቢሮ የተዘጋጀ የ2014 የዜጎች በጀት ሰነድ ነው፡፡ በጣም ቀላልና ግልፅ በሆነ መልኩ እና ለዜጎች ሊረዱት በሚችል ሁኔታ የተዘጋጀ የ2014 በጀት ዓመት ዕቅድ ማስፈፀሚያ በጀት ነው፡፡ ይህ የዜጎች በጀት የሚያብራራው የመንግስት ገንዘብ እንዴት እንደሚሰበሰብ እና የተሰበሰበውን ገንዘብ ለታለመለት ዓላማ ወጪ እንደሚደረግ ቀላል እና ግልፅ በሆነ መልኩ እና ዜጎች ሊረዱት በሚችሉ መልኩ ማሳየት ነው፡፡ ስለሆነም ዜጎች ይህንን ሰነድ ለማገኘትና በሚገባ በማንበብና በመረዳት ለክልል ገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ቢሮ አስተያየትና ጥያቄ ካላቸው ከዚህ በታች ባለው አድራሻ መጠየቅ ወይም ማኛኘት የሚችሉ መሆኑን ለማሳወቅ እንወዳለን፡፡

በሀረሪ ክልል ገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ቢሮ
ህዝብ ግንኙነት ክፍል
ፖስታ ሳጥን ቁጥር 571
ስልክ ቁጥር 0256660955
Website www.dararibof.gov.et
Email-info@hararibof.gov.et